የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፸
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፰ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 70
ADDIS ABABA 26th May 2011

ደንብ ቁጥር ፪፻፳፫/፪ሺ፫
የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...................................................................... ገጽ ፭ሺ፰፻፹፱

**Regulation No. 223/2011**
**Adigrat University Establishment Council of Ministers Regulation ....................................................... Page 5889**

<u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፳፫/፪ሺ፫</u>

<u>ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ ""የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፳፫/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>መቋቋም</u>

፩/ ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል፡፡

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 223/2011</u>

<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF ADIGRAT UNIVERSITY</u>

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. **<u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as the "Adigrat University Establishment Council of Ministers Regulation No. 223/2011".

2. **<u>Establishment</u>**

1/ Adigrat University (hereinafter the "University") is hereby established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
**Negarit Gazeta P.O.box 80,001**

፫. <u>ዋና ግቢ</u>

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በዓዲግራት ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፬. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፰ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. **<u>Main Campus</u>**

The University shall have its main campus at Adigrat and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 26th day of May, 2011.

**MELES ZENAWI**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት